# ተስፋ የሚሰጡ ምልክቶች

ግርማ ካሳ
(muziky68@yahoo.com)
ጥር 30 2001

## መግቢያ

በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ላይ የተወሰደዉ እርምጃ ያላስቆጣዉና ያላበሳጨዉ ኢትዮጵያዊ የለም ቢባል አይገርመኝም። በተለይም አገዛዙ ዉስጥ ደህና ልብ ያላቸዉ ሰዎች ይኖራሉ ብለን እንገምት ለነበርነዉ አንዳንድ ሰዎች እጅግ የሚያሳዝን ነበር። ብርቱካን ሚደቅሳ የታሰረች እለት *«ኢሕአዴግ ዉስጥ ጥሩ ልብ ያላቸዉ ፓርቲዉን ወደ ቀናዉ መንገድ ሊመሩት የሚችሉ ሊኖሩ ይችላሉ የሚል ተስፋ ነበረኝ። አሁንም እነዚህ ሰዎች አሉ ብዬ አስባለሁ። ነገር ግን በዚህ ሳምንት ከታየዉ አሳዛኝ ሁኔታ አንድ በግልጽ የደረስኩበት ድምዳሜ አለ። እርሱም ኢሕአዴግን ወደ ጥሩ አቅጣጫ ሊወስዱ የሚችሉ ኃይላት በፓርቲዉ ዉስጥ ምንም ለዉጥ ሊያመጡ እንዳልቻሉና በነርሱ ተስፋ ማድረግ ከአሁን በኋላ የሚያዋጣ እንዳልሆነ እየታየኝ ነዉ።»* በማለት የተሰማኝን የዉስጥ ሃዘን የጻፍኩትም ለዚህ ነበር።[1]

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ አሁንም በእሥር ላይ ትገኛለች። ሰዉ እንዳያገኛት በጠባብ ክፍል ዉስጥ እንድትቀመጥ ተደርጎ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ጠበቃዋን እንኳን እንዳታይ ተከልክላ ነበር። አራት ኪሎ ያሉ ባለሥልጣናት አሁንም የእብሪት መግለጫ ሲሰጡ ይሰማሉ። በቅርቡ የፍትህ ሚኒስቴሩ አቶ ብርሃን ሃይሉ በፓርላማ ዉስጥ ይህንን ሕግ ወጥ እንስሳዊ ድርጊት ለማሳመን ሲሞክሩ ማየት ምን ያህል ገዢዉ ፓርቲ እንደዘቀጠ ያሳያል።

ይህ እንዲህ እንዳለ አንዳንድ ተስፋ የሚሰጡ ምልክቶችንን ግን ሰሞኑን እያየን ነዉ። ምናልባት ከዚህ በፊት አንዳንዶቻችን እንደደመደምነዉ ሳይሆን ሕወሃት ዉስጥ ያሉ ጥሩ ልብ ያላቸዉ ሰዎች መጠነኛ ግፊት እያደረጉ ሳይሆን እንዳልቀረ አስባለሁ።

## ከሕወሃት ዉስጥ እየተነሳ ያለዉ ተቃዉሞ

እንደሚታወቀዉ የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ መታሰር በሕወሃት ዉስጥ እራሱ ትልቅ ተቃዉሞ እንዳስነሳ በሰፊዉ እየተወራ ነዉ። አቡጊዳ ዲሴምበር 20 2001 እንደዘገበዉ አንዲት የሕወሃት ደጋፊ *«ወደፊት መሄድ ሲገባን ለምን ባለፈ ነገር ላይ ወደ ኋላ እንደሚጎትቱን አይገባኝም።»* ስትል የምትደግፈዉ ገዢ ፓርቲ በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ላይ የወሰደዉን እርምጃ ተቃዉማለች። ሌላ ሕወሃትን የሚደግፉ የትግራይ ተወላጅ አባት ደግሞ *«የሚያስታርቁ ብጹአን ናቸዉ እንደተባለዉ እነፕሮፌሰር ኤፍሬምን አደንቃቸዋለሁ። ነገር ግን እነርሱ የሰሩትን ለአገር የሚጥቅምን ሥራ እያበላሸን ነዉ። አሁን በዚች የልጂ እኩያ በምትሆን ልጅ ላይ የደረሰዉ እጅግ ያሳዝናል። እኔ ያለዉን ነገር እከታተላሁ። ልጅቷ ይቅርታ አልጠየኩም አላለችም። እንደ ሌሎቹም ጦርነት አላወጀችም። ምን አድርጊ ነዉ የሚሏት ? ደግሞም መስፍንንም ቢሆን አዉቀዋለሁ። እርግጥ የፈለገዉን ይናገራል። ማንንም አይፈራም። መንግስቱ ኃይለማሪያምን እንኳን ከስልጣን ወረድ*

---

[1] http://www.abugidainfo.com/amharic/?p=442

*ብሎታል። ግን የሰላም ሰዉ ነዉ። እንግዲህ በኔ እድሜ ነዉ። እንደዚህ በሰደፍ መደብደቡን ስሰማ እኔ እንደተደበደብኩኝ ነዉ የቆጠርኩት።»* ሲሉ የተሰማቸዉን ትልቅ ሐዘን ገልጠዋል።

ከአመራር አባላት ዉስጥ ሁሉ ሳይቀር በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ላይ የተወሰደው እርምጃ ማስተዋል የጎደለዉ፣ በችኮላና በእልህ የተወሰደ ለአገርና ለሕዝብ የማይጠቅምና ገዢዉ ፓርቲን እራሱ የሚጎዳ እንደሆነ በመግለጽ እየተቃወሙት መሆኑን እየሰማን ነዉ። ይህ በራሱ አንድ አበራታችና ተስፋ ሰጪ ምልክት ነዉ እላለሁኝ።

## የአቶ በቀለ ጂራታ መፈታት

አቶ በቀለ ጂራታ የኦሮሞ ፌደራስሊስት ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ ዋና ጸሃፊ ናቸዉ። «ከኦሮሞ ነጻነት ግንባር ጋር ግንኙነት አለህ» ተብለዉ ነዉ እኝህ ሰዉ በግፍ የታሰሩት።

የኦሮሞ ፌደራሊስት ዲምራሲያዊ ንቅናቄ በሕግ የተመዘገበ፣ ሰላማዊ በሆነ መንገድ በኢትዮጵያ ለዉጥ እንዲመጣ የሚፈልግ ድርጅት ነዉ። ብዙ ጊዜ የድርጅቱ ሊቀመንበር ዶ/ር ቡልቻ ደመቅሳ ከፓርላም በስተ ጥግ በኩል ሆነዉ ድርጅታቸዉ በመወከል የሚናገሩት የስለምና የፍቅር የኢትዮጵያዊናትን መልዕክት ነዉ። አንድ ጊዜ እንደዉም «ኢትዮጵጵያ እኮ የኢሕአዴግ ብቻ አይደለችም።፡ኢትዮጵያ የሁላችንም ናት» ሲሉ በጋራ የመስራትን ጥቅም ሲያስረዱ የሰማሁት አባባላቸዉ መቼም አልረሳዉም።

አቶ በቀለ እንግዲህ የዚህ ሰላምዊ ፓርቲ ዋና ጸሃፊ ሆነዉ በሰላም እየታገሉ እንዳለ እየታወቀ፣ መታሰራቸዉ መጀመሪያዉኑ ትክክል እንዳልነበረ ያሳያል። በእኝህ ሰዉ ላይ የተፈጸመዉ በደል ሕገ-ወጥና ጸረ-ዲሞክራሲያዊ ከመሆኑ ባሻገር በምንም መስፈርት ሚዛን የሚደፋ አልነበረም።

ያም ሆኖ ግን አገዛዙ ስህተቱን ተቀብሎ እኝህን ሰዉ መፍታቱ መልካም ዜና ነዉ። ይህ በራሱ ሌላ አንድ አበራታችና ተስፋ ሰጪ ምልክት ነዉ እላለሁኝ።

የአቶ በቀለ ጂራታ መፈታት አንድ እርምጃ ወደፊት እንደመሄድ ተደርጎ የሚታይ ቢሆንም የተለቀቁት በዋስ እንደመሆኑ በአስቸኳይ ክሱ ሙሉ ለሙሉ ተነስቶ ያለአንዳች ፖለቲካ ተጽእኖና እንግልት ሰላምዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴያቸዉን እንዲቀጥሉ መደረግ አለበት።

## የአረና ትግራይ ሕዝባዊ ስብሰባ በመቀሌ

አረና ትግራይ በመቀሌ ታላቅ ሕዝባዊ ስብሰባ አድርጓል። በሺሆች የሚቆጠሩ የመቀሌ ነዋሪዎች አዳራሹን ያጣበቡ ሲሆን ከሕወሃት ሌላ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ እንዲህ አይነት ስብሰባ በትግራይ ሲጠራ የመጀመሪያዉ ነዉ። አንዳንድ አክራሪ የሕወሃት ካድሬዎች በስብሰባዉ ያረጀና ያለፈበት መርዝን ለመርጨትና ስብሰባዉን ለመረበሽ ሞክረዉ ነበር። ግን አልተሳካላቸዉም። አፈረዉ ወጡ። ጥላቻን ለመስበክ መጡ። ህዝቡ ግን ፍቅርን ነዉ የምፈልገዉ አለ።

አቡጊዳ « የአሬና ትግራይ ሊቀመንበር አቶ ገብሩ አስራት ሕወሃት በባደመ ጥይቁ ዙሪያ ነደፎ ያስቀመጠዉን አምስት የ"ሰላም" ሃሳቦች በመቃወም በአዲስ አበበ መስቀል አደባባይ በተዘጋጀዉ ሰላምዊ ሰልፍ ላይ ንግግር ማደረጋቸዉ ያታወሳል። ያኔ ከሌሎች የተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በተጠራዉ ሰልፍ ላይ ያደረጉትን ንግግር በማስታወስ አንድ የሕወሃት ካደሬ «ጠላት ከሆኑት ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ተገኝተዉ ለምን ንግግር አሰሙ?» በሚል ላቀረበዉ

ጥያቄ አቶ ገብሩ ሲመልሱ «ኢትዮጵያዉያንን እስከሆንን ድርስ ትግራይ መሬታችን ነዉ። ኦሮሚያ መሬታችን ነዉ። ደቡብ ና ሶማሊያ መሬታችን ነዉ። አፋርም መሬታችን ነዉ። ለነርሱም ትግራይ መሬታቸዉ ነዉ። አማራም ትግራይ መሬቱ ነዉ። ሊኖርበት ይችላል። በዚህ ማመን አለብን። ከዚህ ዉጭ የፖለቲካ ተቃዋሚ ድርጅቶችን እንደጠላት ለማስፈራሪያ መጠቀም የሥልጣን እድሜን ማራዘሚያ እሆኑ መታወቅ አለበት። አሁንም በሰላምዊ ትግል ካመኑትና ሕጋዊ ፈቃድ ካገኙት ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር አብረን መሥራት እንቀጥላለን።" በማለት ድርጅታቸዉ ከሌሎች የተቃውሚ ድርጅቶች ጋር አብሮ እንደሚሰራና በኢትዮጵያ የመከፋፈል ፖለቲካ ቦታ እንደማይኖረዉ አስረድተዋል።» ሲል ነበር በመቀሌ የታየዉን ተስፋ የሚሰጥ ሌላ ምልክት የዘገበዉ።[2]

እንደዉም እንደሰማሁት ከስብሰባዉ በፊት ሕዝቡ የአረናን ጥሪ እንዳይቀበል ከፍተኛ ቅስቀሳና ማስፈራሪያ ተደርጎ ነበር። ሕዝቡ ግን በድፍረት የስብሰባዉን አዳራሽ ማጣበቡ የሚያሳየዉ የሕወሃት አፍራሽና አክራሪ ፖለቲካ ተቀባይነት እያጣ እንደሆነ ነዉ። ይህም ሌላ ተስፋ የሚሰጥ ምልክት ነዉ።

## ማጠቃለያ

ፈረንጆች "ካሮትና ዱላ" ይሉታል። (Carrots and Sticks) ከገዢው ፓርቲ ዘንድ በማናችዉን ጊዜ የተከፈተ በር ከታየ ፣ ከሚያደርጉት እኩይ ተግባር ተቆጥበዉ ወደ እርቅ ከመጡ ፣ አገራችን ኢትዮጵያን በጋራ በአንድነት ተፋቅረንና ተዋደን እንድንገነባ ፈቃደኛ ከሆኑ፣ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ምህዳሩን ከከፈቱ አብረናቸዉ ለመስራት መዘጋጀት አለብን። ከሁሉም የሚሻለዉ ለሁሉም የሚበጀዉ አማራጭ ይሄዉ ነዉ።

ተስፋ የሚሰጡ አንዳንድ ምልክቶችን በዚህ ጽሁፍ ሳቀርብ በገዢዉ ፓርቲ ዉስጥ ያሉ በአንጻራዊነት ጥሩ ሃሳብ ያላቸዉን ለማበረታታት በማሰብ ነዉ። የመጀመሪያዉ ምርጫችን የሆነዉ «ካሮቱ» እንግዲህ ይህ ነዉ።

ታዲያ ተስፋ የሚሰጡ አንዳንድ ምልክቶችን ብናይም አሁንም መገንዘብ ያለብን መሰረታዊ ሃቅ አለ። በሕወሃት ያሉ ጥቂት አክራሪዎች አሁንም አገሪቷን እንደፈለጉ እያሽከረከሩ ናቸዉ። አሁንም ህዝባችንን እያመሱት ነዉ። ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ይኸዉ አሁንም ከታሰረች 36 ቀናት ሲሆናት ቴዲ አፍሮ 356 ሆኖታል። በቀለ ጄራታ በዋስ ቢፈታም ነገ ተመልሶ ሊታሰር ይችላል። ሌሎችም የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች በማናቸዉም ጊዜ ወህኒ ሊወርዱ ይችላሉ።

የሕዝባዊ ስብሰባዎች መደረግ፣ የእሥረኞች መፈታት በአዎንታዊነት የምንቀበለዉ ቢሆንም ችግራችንን ከሥሩ እስካላስወገድን ድረስ ልንዘናጋ ልንተኛ አይገባም።

ስለሆነም ለዲሞክራሲ ለሰላም ለአገራችን አንድነትንና ሉዓላዊነት የሚደረገዉን ትግል በተጠናከረ መልኩ መቀጠል ይጠበቅብናል። ሕግ የበላይ እስኪሆን፣ የዜጎች መብት ሙሉ ለሙሉ እስኪከበር፣ ህዝብ በመረጠዉ እስኪተዳደር፣ የሰራዊት አባላት ለግልሰሰብ ሳይሆን ለህዝብ እስኪገዙ፣ በወገንና በወገን መካከል የተተከለዉ የጥላቻ ግድግዳ እስኪፈርስ፣ አገራችን የባህር ወደ እስክታገኝ፣ የተገነጠለችዋ ኤርትራ ከእናት አገሯ በሰላም እስክትቀላቀል፣ ህዝባችን ከልመናና ዉርደት

---

[2] http://www.abugidainfo.com/amharic/?p=390

እስኪላቀቅ፣ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በልቶ እስኪያደር፣ ወ/ት ብርቱክንና ሌሎች የታሰሩ የሕሊና እሥረኞች እስኪፈቱ .. ትግላችን ይቀጥላል። የሕዝብን ፈቃድ አልሰማም የሚሉና ሕዝብ ወደሚፈለገው ግብ እንዳይደርስ መሰናክል የሚሆኑ አካላትም ካሉ እነርሱን ከማስወገድ ዉጭ ሌላ አማራጭ አይኖርም። "ዱላው" እንግዲህ ይህ ነዉ።

እጃቸዉን ለሰላም ከተዘረጋ እኛም እንዘረጋለን። እጃቸው ለመግደልና ለማሰር ከተዘረጋ ....
መልሱን ለአንባቢያ እተዋለሁ።